የጽዮን ከብር ቤተ ክርስቲያን

# ቅድስና ለእግዚአብሔር

"እኔ ቅዱስ ነኝና ተቀደሱ"

asfaw bekele
9/1/2010

## ጥናት 1

**ርዕስ ፥ ተቀደሱ 2ዜና.29፥1-11**

**ዓላማ ፥ቅዱስና ከእግዚአብሔር ሕዝብ የሚጠበቅ እንደሆነና ያለ ቀደስ ግን ቁጣና መቅሰፍትን እንደሚያመጣ ለማሳየት ነው።**

**መግቢያ፥ ሕዝቅያስ የእግዚአብሔርን ቤትና ህዝቡን ለመቀደስ የወሰደውን እርምጃ ከክፍሉ እንመለከታለን።**

## ጥያቄዎች

1. በክፍሉ መ- መሪያ ስለ ሕዝቅያስ ምን ተነገረ?
2. ቅን ነገርን ማድረግ ምን ማለት ነው?
3. ሕዝቅያስ እንደነገሠ በመ- መሪያ ያደረገው ምንድነው? ለምን?
4. ህዝቅያስ ሌዋውያንን ሰብስቦ ምን አላቸው? ለምን እነርሱን ብቻ ሰበሰበ? ብለህ ታስባለህ?
5. በቀደመው ዘመን አባቶቻችሁ ምን አደረጉ? ውጤቱስ ምን ነበር? ከዚህስ ስለ እግዚአብሔር





በግልህ በተለየ መልኩ እግዚአብሔር በየት ው ጥናት ተናግሮሃል? ይህስ በህይወትህ ያመጣው ለውጥ ለምንድነው?

6. ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አገልግሎት በቡድኖችም ሆነ በአጠቃላይ በቤተክርስቲያን ውስጥ ፍሬያማ ይሆን ዘንድ ምን ትጸልያለህ?

# የማጠቃለያ ጥናት

**ጥያቄዎች፥**

1. ከተጠኑት ክፍሎች ውስጥ በቃል የያዝካቸውን ርዕሶች ተናገር
2. በአጠቃላይ በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዲሁም በክርስቲያን ግላዊ ህይወት መቀደስ /ቅድስና/ የሚያስከትለውን በረከትና አለመቀደስ ደግሞ የሚያስከትለውን ውጤት ዘርዝር ተወያዩበት።
3. በአማኝ ህይወት ኀጢአት የሚነግስበትና የሚመክርበት ምን ሲሆን ነው? ሮሜ.6፥12
4. አሁን ባለንበት ዘመን የሚያምኑ ከማያምኑ ጋር ያላቸው በተግባር የሚታይ ችግር ምን ይመስላል? ይህስ አሁን ባለችው ቤተክርስቲያን ያስከተለው በተግባር የሚታይ ችግር ምንድነው? /በስፋት ተወያዩበት/
5. ከነዚህ ከተጠኑት ዘጠኝ ጥናቶች ውስጥ ለአንተ





አሠራር ምን ተረዳለህ?

6. የእግዚአብሔር ቁጣ ከህዝቡ እንዲመለስ ህዝቅያስ ምን ማድረግ ፈለገ? ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ማድረግ ማለት ምን ማለት ነው?
7. በቁጥር 11 ላይ ህዝቅያስ ስለ ሌዋውያን መመረጥ ምን ተናገረ? ቸልተኝነት ቅድስናን እንዴት ያበላሻል?

**ማዛመድ፥**

- ከንጉሥነት ሥራው ቅድሚያ የእግዚአብሔርን ቤት አገልግሎት ማስቀደሙን ስታይ ከዚህ ምን ትማራለህ?
- መቀደስ በረከት አለመቀደስ መረገም እንዳለበት ምን ያህል ተረዳህ? አካፍል።
- ለቅድስና የጠራህ እግዚአብሔር መሆኑን አውቀህ ምን ያህል በፊቱ በትጋት ትመላለሳለህ?

## ጥናት 2

**ርዕስ፥** ራስን ማቅረብ መቀደስ ሮሜ.6፥12-19

**ዓላማ፥** በክርስቶስ ኢየሱስ ከሞት ተለይቶ ህይወትን የተቀበለው አማኝ ለእግዚአብሄር በመታዘዝ የተቀደሰ ኑሮ መኖር እንዳለበት ለማሳየት።

**መግቢያ፥** ሐዋርያት ጳውሎስ በክርስቶስ አዲስ ሕይወትን ላገኙት ለሮሜ ሰዎች እንዴት መኖር እንዳለባቸው የጻፈውን እንመለከታለን።

**ጥያቄዎች፥**

1. በአማኝ ሕይወት ኀጢአት የሚነግሰው መቼ ነው? /ቁ.12/ አማኝ ብልቶቹን ለምን ለምን ሊያውል ይችላል? /ቁ.13/
2. ብልቶቻቸውን ለእግዚአብሔር ማቅረብ ያለባቸው ለምንድን ነው? ከሙታን ተለይቶ በህይወት መኖርና መቀደስ ምን ግንኙነት አለው?
3. ከጸጋ በታች መሆናችን ከምንኖረው ሕይወት ጋር ያለው ዝምድና ምንድነው?



መሪ ርዕስ፥ "እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ"
1ጴጥ.1፥15

4. "የአዲስ ኪዳን መካከለ " ሲል ምን ማለቱ ነው? ክርቶስ የአዲስ ኪዳን መካከለ የሆነው ለምንድነው?
5. በቁ.22 "ደም ሳይፈስ ስርየት የለም" የሚለውን ሃሳብ እንዴት ትረዳዋለህ? ዕብ.9፥20 በህያው ቃል ትርጉም አንብቡት
6. ኀጢአትን ለመሻር ራሱን በመስዋዕት የተገለጠው ኢየሱስ ዳግመ በእንዴት ያለ ሁኔታ ይገለጣል? ለምንስ ነው የሚገለጠው?

**ተዛምዶ፥**

- አንተስ ህሊናህን ከሞተ ሥራ በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ለማንጻት በቅድስና እግዚአብሔርን ምን ያህል ታመልከዋለህ?
- የሚጠባበቁትን ያድናቸው ዘንድ ደግሞ የሚገለጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን በቅድስና ለመኖር ምን ያህል እየጠበቅከው ነው? ራስህን ተመልከተው?

# ጥናት 9

**ርዕስ፥** ህሊናን ከሞተ ሥራ የሚያነጻ የከበረ ደም

ዕብ.9፥11-23

**ዓላማ፥** የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከሞተ ስራችን ህቃናችንን ለማንጻት እግዚአብሔር አማላካችንን ልናመልክ እንድንችል እንደሚያደርገን ለማሳየት

**መግቢያ፥** በገዛ ደሙ ወደ እግዚአብሔር ህልውና የዘላለም ሊቀካህን ደሙ የሚያከናውነውን ህሊናን የማንጻት ስራ በዛሬው ጥናታችን እንመለከታለን

**ጥያቄዎች፥**

1. ሊቀካህኑ ክርስቶስ የገባበት ቤተመቅደስ ምን አይነት ነው?
2. በክርስቶስ ወደ ቅድስት የገባበት ሁኔታ እንዴት ነበር?
3. በቁ.14 መሰረት የክርስቶስ ደም የሚሰራው ሥራ ምንድነው? ለምን? የህሊና ከሞተ ሥራ መንጻት ቅድስናና እግዚአብሔርን ማምለክ እንዴት ይያያዛሉ?





4. አማኝ ብልቶቹን የምንና የምን ባሪያ ሊያደርጋቸው እንደሚችል ተገልጾ ታያለህ?
5. ከኀጢአት አርነት መውጣታችንን እንዴት ልናጸናው እንችላለን?
6. በክፍሉ ውስጥ "አታቅርቡ" "አቅርቡ" ከሚሉት ቃላት ስለ ምርጫና ኀላፊነት ምን ትረዳለህ?

**ተዛምዶ፥**

- በክርስቶስ ያለከው አንተ ዛሬ ህይወትህን ስትመረምር ባሪያነትህ ለማን ሆኖ አገ ከው?
- ቀደም ሲል ያለ ክርስቶስ በነበርክበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ ለአመጻ ራስህን ሰጥተህ እንደነበር ዛሬስ ለጽድቅ ራስህን ሰጥተኃል ወይ?
- የእግዚአብሔር ጸጋ ሊረዳህ ከአንተ ጋር ስላለ ራስህን በቅድስና ልታኖር ኀላፊነት እንዳለብህ ምን ያህል አስተዋልክ?

## ጥናት 3

**ርዕስ ፥** ራስን ከአመጻ መጠበቅ 1ዮሐ.3፥1-10

**ዓላማ፥** አማኝ የእግዚአብሔር ልጅ መሆንና ኃጢአትን መሥራት ሊጣጣሙ እንደማይችሉ በማወቅ ለተሰፋው ፍጻሜ ለመድረስ ራሱን ከአመጽ መጠበቅ እንዳለበት ለማስገንዘብ።

**መግቢያ፥** በእግዚአብሔር ፍቅር ልጅነትን የተቀበሉ ትክክለ አኗኗር እንዴት መሆን እንዳለበት የሚያሣየውን ክፍል እንመለከታለን።

**ጥያቄዎች፥**

1. በክፍሉ መ- መሪያ የአማኞችና የእግዚአብሔር ሕብረት በምን መልክ ተገልጧል? ይህንን ልጅነት ስላገ ንበት ፍቅር ሲናገር እንዴት ትረዳዋለህ?
2. ይህንን ልጅነት ያገ -ት አማኞች ጌታ ሲገለጥ ምን እንደሚሆን ይናገራል? ኑሮአቸውስ ምን ሊሆን ይገባል?





4. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እ ነፍሱን አሳልፎ የሰጠው ለምንድነው?
5. ይህ ክርስቶስ ነፍሱን የከፈለለት የራሱ ህዝብ የእግዚአብሔር አላማ በህይወቱ እንዲፈጸም ሊያደርገው የሚገባው የእርሱ ድርሻ ምንድነው?

**ተዛምዶ፥**

- እግዚአብሔር በልጁ በኩል የገለጠው ጸጋ የሚያድን በቅድስና የሚያኖርና የክርስቶስን ምጽአት በትእግስት እንድንጠባበቅ የሚያደርግ መሆኑን ስትመለከት ይህን ጸጋ ምን ያህል ታከብረዋለህ?
- የቅድስና ህይወት መንፈስ ቅዱስ በእ ውስጥ የሚሰራው ህይወት ቢሆንም እንኳ አንተም ራስህን በመግዛት እግዚአብሔርን በመፍራትና ለመንፈስ ቅዱስ በመታዘዝ ይህ የቅድስና ህይወት በግልህ እንዲገለጥ ለማድረግ ድርሻ እንዳለህ ምን ያህል ተገነዘብክ?
- በጸጋ የተሞላ ህይወት ከመኖርህ የተነሳ የክርስቶስን የቅድስና ባህርይ ምን ያህል እየተገለጠብህ ነው?

# ጥናት 8

**ርዕስ፥** በቅድስና የሚያኖር ሰማያዊ ጸጋ ቲቶ.2፥11-15

**ዓላማ፥** ከእ በኩል ከሚገኝ ሞራላዊ ባህርይና ሃይማኖታዊ ድርጊት ውጪ መዳንን ያገ ንቸት እግዚአብሔር በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የገለጠው የመዳን ጸጋ በክርስቶስ ስንኖር በእ ውስጥ የሚሰራውን የቅድስና ህይወት ለማሳየት።

**መግቢያ፥** በዛሬው ጥናታችን እግዚአብሄር ለሰው ልጅ የገለጠው ጸጋ ለአማኞች ህይወት የሚሰራውን ስራ እንመለከታለን።

**ጥያቄዎች፥**

1. ጸጋ ምንድነው? በስፋት ተወያዩበት
2. ይህ የተገለጠው ሰማያዊ ጸጋ የሚሠራቸው ሥራዎች ዘርዝር
3. የእግዚአብሔር ጸጋ የሚያድን, በቅድስና እንድንኖርና የኢየሱስን ክብር መገለጥ በትዕግስት እንድንጠብቅ የሚያደርገን እንዴት ነው?





3. ከቁ.6-10ስ ለ እግዚአብሔር ልጆችና ስለ ዲያቢሎስ ልጆች በማነጻጸር የሚናገረው ምንድነው?
4. በእርሱ የሚኖሩ ሁሉ ኀጢአትን አያደርግም የሚለውን እንዴት ትረዳዋለህ? ኀጢአትን የሚያደርግ ሁሉ አላየውም አላወቀውምም ለምን ተባለ?
5. ከእግዚአብሔር የተወለደ ኃጢአትን የማይሰራው ከምን የተነሳ ነው ይላል? ስለ ዘር የምታውቀውን ዘርዝር

**ማዛመድ፥**

- ኀጢአትን ሊያስወግድ የተገለጠውን ክርስቶስን ተቀብለህ ስትኖር የየእለተ ኑሮህ ያለ ኀጢአት መሆን እንዳለበት አስተውለሃልን?
- ኀጢአት የዲያቢሎስ መሆኑን ስታስብ ኃጢአትን ላለመስራት ምን ያህል ትሸሻለህ?
- ዘር በውስጡ ያለውን ባህርይ በእድገት እንደሚገልጥ ሁሉ በውስጥህ ላለው የእግዚአብሔር ዘር ባህርይ መገለጥ ምን ያህል መልካም እርሻ ሆነህለታል?

## ጥናት 4

**ርዕስ፥** ለእግዚአብሔር መለየት 2ቆሮ.6፥14

**ዓላማ፥** የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነውና ልጅነትን የተቀበለው በቅድስና ሕይወት ሊያድግ እንጂ በዚህ ዓለም ካሉ ርኩስ ነገር ጋር ህብረት ሊያደርግ እንደማይገባው ለማስገንዘብ።

**መግቢያ፥** ሐዋሪያው ሁለት ሊዛመዱ የማይችሉ ነገሮችን በማወዳደር አማኝ ሊኖረው ስለሚገባ ትክክለ አረማመድ የጻፈውን እንመለከታለን።

**ጥያቄዎች፥**

1. የሚያምን ከማያምን ጋር በምን መልክ ህብረት እንዳያደርጉ ያስጠነቅቃል? የማይመታች አካሄድ ምንድነው ትላለህ? ምሳሌ ስጥ
2. ሁለቱን የተነጻጸሩትን ሃሳቦች ዘርዝር
3. የማያምን ከሚያምን ለምን የዚህን ያህል የተራራቀ ነገር አላቸው ትላለህ?
4. እ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ነን ሲል ምን



መሪ ርዕስ፥ "እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ"
1ጴጥ.1፥15

**ተዛምዶ**

- በማስተዋልና በመጠን በመኖር ጌታ ኢየሱስ ሲገለጥ ልታገ ው ያለውን የእግዚአብሔርን በረከት ምን ያህል ትጠባበቃለህ?
- አሁን ያለህን ህይወት ስትመረምር የጠራህ ቅዱስ መሆኑን እለተ እለት በመገንዘብ ምን ይህል የተቀደሰ ህይወት ትኖራለህ?
- እግዚአብሄር የልጁን ደም የከፈለልህ አንተን ከስንቱ የህይወት ጎዳናህ ለማዳን መሆኑን በመረዳት የተቀደሰ ህይወትን በመኖር ይህን ደም ምን ያህል ታከብረዋለህ?
- ግብዝነት የሌለበትን ፍቅር ለወንድሞች በመግለጥና ከጥላቻና ከበቀል ነጻ በመሆን የቅድስና ህይወትን ምን ያህል ትጠብቃለህ?

ታጥቃችሁ በመጠን ኖራችሁ" የሚሉትን ሃረጎች እንዴት ትረዳቸዋለህ? ይህስ የክርስቶስን መገለጥ እንደሚገባ ለመጠባበቅ ምን አስተዋፅኦ አለው?

2. ሰዎች እውነትን ከማወቃቸው በፊት ምን አይነት ኑሮ መኖር አለባቸው ይላል? /ቁ.15-17/
3. ጴጥሮስ እውነትን ያወቁ ሰዎች /አማኞች/ እንዴት መኖር አለባቸው ይላል? /ቁ.15-17/ --መቀደስ /ቅዱስ መሆን/ ማለት ምን ማለት ነው? እንዴትስ መቀደስ ይቻላል?በዚህ እንግዳና መጻተ መሆንን በህይወት ዘመን ሁሉ መረዳት ለመቀደስ እንዴት ይጠቅማል?
4. እግዚአብሔር ነውርና እድፍ የሌለበት የልጁን የኢየሱስን ክርስቶስን ደም የከፈለላቸው ለምንድነው?
5. እነዚህ አማኞች እርስ በርሳቸው ሊኖራቸው ስለሚገባ የወንድማማች ህብረት ጴጥሮስ ምን ይላቸዋል? የግብዝነት ፍቅር በወንድማማች ህብረት ውስጥ ሲኖር ቅድስናን እንዴት ያረክሳል?





ማለቱ ነው? ስለመቀደስ የምታውቀውን ተናገር።

5. ሐዋርያው እግዚአብሄር ምን እንደተናገረ ይናገራል?
6. ውጡና የተለያችሁ ሁኑ የሚለው አባባል ከማያምኑ ጋር ፈጽሞ ህብረት ሊኖረው አይገባም ማለት ነው? ለምን?
7. እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ የተቀበለው አማኝ እንዴት እንደሚመላለስ ይናገራል? ላድስናን ፈፅም እያደረግን ሲል ምን ማለቱ ነው?

**ከሕይወትህ ጋር አዛምድ**

- መልካሙን ጸጋህን ከሚያጠፋና ሥጋና መንፈስህን ከሚያረክስ ከንቱ ከሆነ ዓለባዊ ህብረት የቱን ያህል ራስህን ትጠብቃለህ?
- በኑሮህ አንተ የተቀደሰው የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንደሆንክ ምን ያህል ልብ ብለሃል?

## ጥናት 5

**ርዕስ፥** "ከዝሙት ራቁ" 1ተሰ.4፥1-8

**ዓላማ፥** ጳውሎስ የተሰሎንቄን አማኞች እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰ ውን ኑሮ እንዲኖሩ ሲመክር የጻፈላቸውን እናያለን።

**ጥያቄዎች፥**

1. ሐዋርያው በጻፈበት ጊዜ የተሰሎንቄ አማኞች ህይወት ምን ይመስል ነበር? ምንስ ይመክራቸዋል, ይለምናቸዋልም?
2. የእግዚአብሔር የሆነውና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰ ው ትዕዛዝ ምንድነው? መቀደስ ማለት ምን ማለት ነው?
3. ከክፍሉ አንጻር ቅድስና እንዴት ባለ መልክ ተገልጿል? ከዝሙት መራቅ/መሸሽ/ ለምን ያስፈልጋል ትላለህ?



**መሪ ርዕስ፥ "እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ"**
**1ጴጥ.1፥15**

## ጥናት 7

**ርዕስ፥** "ቅዱሳን ሁኑ"

**ዓላማ፥** እግዚአብሔር በዘላለማዊ ባህርይ ቅዱስ እንደሆነ ሁሉ በክርስቶስ ኢያሱስ የተዋጁትን ልጆቹን ደግሞ እንደዚሁ ከኀጢአትና ከርኩሰት በመራቅ ለእግዚአብሔር የተለየ ህይወት መኖር እንዳለባቸው ለማሳየት

**መግቢያ፥** በዛሬው የጥናት ክፍላችን ሐዋርያው ጴጥሮስ በተለያዩ ሃገሮች ለተበታተኑት አማኞች ሊኖሩ ሰለሚገባቸው መንፈሳዊ ሕይወት የተናገረውን ቃል እንመለከታለን።

**ጥያቄዎች፥**

1. በዚህ ክፍል ክርስቶስ ኢየሱስ ሲገለጥ ልናገ ው የሚገባንን የእርሱን በረከት እንዴት መውሰድ እንዳለብን ይናገራል? "የልቡናችሁን ወገብ

መሆኑን የቱን ያህል አስተዋልክ?

10. አመጸ ውን በሞት ለመቅጣት የእግዚአብሔር ፍርድ ስታይ ከኃጢአት መንገድ ባትመለስ ምን ሊገጥምህ እንደሚችል ተገነዘብክ?

© Pastor Asfaw Bekele., Vancouve, Canada 

መሪ ርዕስ፥ "እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ"
1ጴጥ.1፥15

4. ከዝሙት ጠንቅ የተነሳ ጌታ ስለዚህ ነገር የሚበቀል ነው ሲል ለዚህ ማስረጃ የሚሆን ከመጽሐፍ ቅዱሳችንም ምን ታሪክ መጥቀስ ትችላለህ? አሁን ከሚታየው የዓለማችንና የአካባቢያችን ሁኔታስ? እግዚአብሔር ኃጢአትን መንቀል ለምን አስፈለገው ትላለህ?
5. ይህንን ቃል መስማትና ለመታዘዝ ፈቃደ ስላልሆነው ሰው ምን ትላለህ? መንፈስ ቅዱስን የጣለ ነው ሲል ምን ማለቱ ነው?
6. በእግዚአብሔር ፈቃድ በቅድስና ለመኖርና ባለመኖር ያለውን ውጤት ከክፍሉ ምን አየህ? እግዚአብሔር ከዝሙት የተነሳ የቀጣቸውን ሕዝብ ስታይና ስታስብ አንተስ ራስህ ምን ያህል ከዚህ ኃጢአት ትጠበቃለህ?
7. የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነውን አካላችንን ለዝሙት አሳልፈን ብንሰጥ በውስጣችን ያለውን መንፈስ ቅዱስን መቃወምህ መሆኑን የቱን ያህል ታስተውላለህ? ከዚህ ክፍል ሌላ የተማርከው ነገር አለ?

© Pastor Asfaw Bekele., Vancouve, Canada 

## ጥናት 6

**ርዕስ፥** እርም የሆነውን ነገር አስወግድ ኢያሱ 7፥1-15

**ዓላማ፥** አማኝ በግል ሕይወ ኃጢኣት ሲኖር እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደማይሆንና ይህም በህይወቱ አሸናፊነትን እንደሚያሳጣው ለማስገንዘብ።

**መግቢያ፥** ኢያሪኮን ድል ነስቶ ወደ ፊት በመገስገስ ጋይን ለመያዝ የሄደው የእስራኤል ጦር የገጠመው ነገርና ምክንያቱን ከዚህ ክፍል እንመለከታለን።

**ጥያቄዎች፥**

1. በክፍሉ መ- መሪያ እግዚአብሔር እስራኤልን ለምን ተቆጣ? ከክፍሉ አንጻር እርም ማለት ምን ማለት ነው? /ምዕ.6፥19/ ኃጢአትን የሰራው አንድ ግለሰብ ሲሆን ቁጣው ለምን በማህበራት ሁሉ ላይ ሆነ ትላለህ?
2. በመካከላቸው እርም መኖሩን ያላወቀው ኢያሱ ጋይን





ለመያዝ ምን ሲያደርግ ይታያል?

3. በጋይ ሰዎች መሸነፋቸው /መመታታቸው/ በኢያሱ በሽማግሌዎችና በህዝቡ ልብ ምንን ፈጠረ? ምንስ ሲሉ ይታያል? /ቁ.4-9/
4. በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ተደፍቶ ለነበረው ኢያሱ እግዚአብሔር ምን ይለዋል?
5. በቁ.12 እግዚአብሔር የተናገረውን ስትመለከት ስለ ኃጢአት አስከፊነት ምን ትላለህ?
6. ኢያሱ ምን እርምጃ እንዲወስድ ይናገረዋል? እርቡ ለሚገኝበት ሰው የሚሰጠው ብያኔ ምንድነው? ለምን?
7. የአንድ ሰው በደል አንድን ህዝብ ሙሉ ማስጨነቁን ስታይና በጠላታቸው መሸነፋቸውን ስታይ እንዴት ባለ መንገድ መራመድ ይገባል ትላለህ?
8. አንተ በግልህ ኃጢአትን መስራትህ አንተን ብቻ ሳይሆን የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተክርሰቲያንን እንደሚያስጨንቃተ የቱን ያህል አየህ?
9. በህይወትህ ተሸናፊ ከሆንክና አሸናፊነትን ካላየህ አንዱና ምናልባትም ዋነ ው ምክንያት ኃጢአት